


# City View

ክረምት 2022-23

ፎቶ፡ Kyle Klein


## የካምብሪጅ የውሃ መምሪያ ዘላለማዊ ኬሚካል የሆነውን PFASን በንቃት መታገል

per- እና polyfluoroalkyl ንጥረ ነገሮች (PFAS) በስማቸው ብቻ በመመስረት፣ በእርግጠኝነት በሳንድዊች መጠቅለያዎ ውስጥ ማግኘት የሚፈልጓቸው ንጥረነገሮች አይደሉም። ግን በቅርብ ጊዜ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በሁሉም ቦታ - በፒዛ ሳጥንዎ፣ በመዋቢያ ቦርሳዎ እና ምናልባትም በልብስዎ ውስጥ አሉ።

PFAS በሰፊው ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆን ረጅም ጊዜ የሚቆዩ፣ በጊዜ ሂደት በጣም በዝግታ የሚበሰብሱ ኬሚካሎች ናቸው። እንዲያውም "ዘላለማዊ ኬሚካሎች" ተብለው ሲጠሩ ሰምተው ይሆናል። በአካባቢያቸው በስፋት ጥቅም ላይ በመዋላቸው እና በመቆየታቸው የተነሳ፣ PFAS አሁን በውሃ፣ በአየር፣ በአሳና በአፈር ውስጥ በመላ አገሪቱ እና አለም ላይ ይገኛሉ።

በተለያዩ ምርቶች ውስጥ የሚገኙት በሺዎች የሚቆጠሩ የ PFAS ኬሚካሎች የሰው ልጆችን ጤና እና የአካባቢ አደጋዎችን ማጥናት እና መገምገም አዳጋች ያደርጉታል። በ PFAS ውህዶች የረዥም ጊዜ አጠቃቀም የተነሳ፣ በመላው አገሪቱ በሕዝብ የመጠጥ ውሃ ሥርዓቶች ውስጥ እነዚህን ዘላለማዊ ኬሚካሎች ማግኘት አያስደንቅም። እንደመታደል ሆኖ ለካምብሪጅ ነዋሪዎች፣ ማሳቹሴትስ በሀገሪቱ ውስጥ ለመጠጥ ውሃ በጣም ጥብቅ ደንቦች አሉት። በ2020፣ የማሳቹሴትስ የአካባቢ ጥበቃ መምሪያ (MassDEP) ከጃንዋሪ 1፣ 2021 ጀምሮ በስራ ላይ የዋለውን የPFAS ደንብ አወጀ። ደንቡ ስድስት የተወሰኑ የ PFAS ውህዶች ሩብ አማካይ በየትሪልየኑ (ppt) ከ20 ክፍል መብለጥ እንደሌለበት ነው።


*በገጽ 2 የቀጠለ*




## የከተማ አስተዳዳሪው መልዕክት



በሴፕቴምበር ወር እንደ የከተማ ስራ አስኪያጅነት ስራ ከጀመርኩ ሁለት ፈጣን ወራቶች አልፈውኛል! ስሜቴን የሚገልጹት ምርጥ ቃላቶች ጉልበት እና ብሩህ ተስፋ ናቸው። በጣም ልዩ እና አስገራሚ ማህበረሰብ ነን፣ እናም ሁለቱንም የሚያጋጥሙንን እድሎችና ተግዳሮቶች ለመፍታት ጓጉቻለሁ።

ለኔ ቅድሚያ ሰጥቼው የነበረው ነገር ከተማችን በተሳለጠ መንገድ እንድትቀጥል የሚያደርጉትን እና የተሻለ ለማድረግ ጠንክረው እየሰሩ ያሉትን ሰዎች ማወቅ ነው። በከተማችን መሪዎችና ሰራተኞች ትጋት እና እውቀት በጣም ተደንቄያለሁ። እውነታው ግን ልክ እንደሌሎች ድርጅቶች ሁሉ፣ እኛም ከሁለት ዓመት በላይ ወረርሽኙን ከታገልን በኋላማድረግ እየፈለግን ያልቻልነው አለ። በተለይም በከተማው ምክር ቤት እና በህብረተሰባችን የተቀመጠውን ታላቅ አጀንዳ ለማሳካት በምንፈልግበት ወቅት ይህ ጊዜ ባህላችንን የምናድስበት ወሳኝ ወቅት ነው። መሪዎቻችንን የበለጠ ለማብቃት፣ ለሰራተኞቻችን ደህንነትን እና የስራ/ህይወት ሚዛንን ለማሻሻል እና ለፀረ-ዘረኝነት፣ ልዩነት፣ እኩልነት እና ማካተት ያለንን ቁርጠኝነት ለመቀጠል ኢንቨስት ለማድረግ በጉጉት እጠባበቃለሁ።

ከተማችን ያከናወነችውን አንዳንድ አስደናቂ ስራዎች ለማጉላት እፈልጋለሁ። ከፖሊስ አመራር ጋር ግማሽ ቀን ያሳለፍኩኝ ሲሆን በመምሪያው ውስጥ ባለው ቁርጠኝነትና መንፈስ በጣም ኩራቴ ነው የመጣሁት። ከ10 ዓመታት በላይ የካምብሪጅ ፖሊስ በሂደት ላይ ባሉ የመመሪያ ማሻሻያዎች ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ አፍስሷል ይህም ቀጣይነት ያለው ጥረት ተጨባጭ ውጤቶችን አስገኝቷል። የካምብሪጅ ፖሊስ


*በገጽ 2 የቀጠለ*



የነዳጅ እርዳታ ፕሮግራም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ነዋሪዎች ያግዛል
ገጽ 3



ክረምት እየመጣ ነው። ዝግጁ ነዎት?
ገጽ 4-5



የካምብሪጅ የእሳት አደጋ መምሪያ የቤት ውስጥ የእሳት አደጋ ትምህርት ቤትን ይዞ ተመልሷል
ገጽ 6




ዋና ዋና ዜናዎች በበርካታ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል
ገጽ 9-15

**ዘላለማዊ ኬሚካል የሆነውን PFASን በንቃት መታገል** *ከሽፋን የቀጠለ*

## ካምብሪጅ ምን እየሰራ ነው?

የካምብሪጅ የውሃ መምሪያ (CWD) በኦገስት 2019 ለPFAS በፈቃደኝነት ናሙና መውሰድ የጀመረ ሲሆን እንዲሁም የ"PFAS ቅነሳ እቅድ" ማዘጋጀት ጀምሯል። በካምብሪጅ የ PFAS ስብስቦች ውስጥ ወቅታዊ ልዩነት ያለ ሲሆን ከፍተኛ መጠን ያለው ክምችት በበጋው ወራት መጨረሻ ላይ እና ዝቅተኛው በቀዝቃዛው የክረምት ወራት ውስጥ ነው። ከ MassDEP ድጋፍ የ PFAS ክምችቶችን ለመቀነስ የተለያዩ የማጣሪያ መንገዶችን ውጤታማነት ለመፈተሽ የ bench scale (ቤንች ስኬል) የሙከራ ጥናት ተዘጋጅቶ ነበር። ያ ጥናትም በ2021 መጨረሻ ተጠናቀቀ። ውጤቶቹ ግራኑላር አክቲቬትድ ካርቦን (GAC) የካምብሪጅ PFAS ክምችትን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ ረገድ ለCWD ምርጡ ዘዴ መሆኑን ወስነዋል።

GAC፣ንጥረነገሮች በቅድመ ማከሚያ ዘዴዎች ከተወገዱ በኋላ በፍሰት ማጣሪያ ሁነታ ውስጥ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ PFASን ከመጠጥ ውሃ በተሳካ ሁኔታ እንደሚያስወግድ አሳይቷል። ማጣሪያዎቹ ሁልጊዜ የካምብሪጅ ኦፕሬሽን ንድፍ አካል ናቸው። በግንባር ቀደምነት PFAS፣ ከዚያም ብቅ እያሉ ያሉ የጤና አደጋዎች እና እየከረሩ በመምጣት ላይ ያሉ ደንቦች ባሉበት ወቅት CWD የ GAC ለውጥ ማድረግን የመከላከያ የጥገና ልምድ አድርጎ ወደ ፊት ይራመዳል። በተለይም አሁን በ PFAS በመላ አገሪቱ የከርሰ-ምድር እና የገጸ-ምድር የውሃ አካላት ውስጥ መገኘት ሳብያ፣ የማጣሪያ መንገዶች ለውጦች የሚመከሩ መስፈርቶች ናቸው። የGAC ማጣሪያን መለወጥ Brita (የሚያጣራ የውሃ መያዣ ጆግ) ወይም የቤት ውስጥ ማጣሪያን ከመለወጥ ብዙም የተለየ አይደለም። ከተወሰነ ጊዜ ወይም ከተወሰነ መጠን በኋላ ማጣሪያውን ይለውጣሉ። ልዩነቶቹ የCWD ማጣሪያዎች በቦታቸው የተቀመጡ መሆናቸው እና የማጣሪያ ለውጥ ለማድረግ በቀላሉ በማጣሪያው ውስጥ ያለውን አሮጌ ካርበን በአዲስ ካርበን መለዋወጡ ነው።

በ2022 ጸደይ፣ CWD በ 6 ማጣሪያዎቹ ውስጥ የማጣሪያ መንገዱን ለመተካት ጨረታ አውጣ እና ውል ሰጠ። ፕሮጀክቱ በዚህ በጋ እንዲጀመር ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በኮቪድ-19 ወረርሽኝና በአቅርቦት ሰንሰለት ጉዳዮች፣ የማምረት፣ የማድረስ እና የየመግጠም ሂደቶች ተስተጓጉለው እስከ በልግ ድረስ በከፍተኛ ሁኔታ ዘግይቷል። የCWD የመጀመሪያው የኦገስት 2022 የPFAS ውጤት ከ20 ppt በላይ ሲመጣ እና በኋላም ተቀባይነት ሳያገኝ ሲቀር፣ ወደ የማሳቹሴትስ የውሃ ሃብት ባለስልጣን (MWRA) ለመቀየር በኦገስት 30፣ 2022 ተወስኖ ተከናውኗል። በ2019 PFAS በካምብሪጅ ውሃ ውስጥ መኖሩ ተለይቶ ከታወቀ ጀምሮ CWD የግዛት እና የፌደራል መመሪያዎችን እና ተከታዩን ደንብ በማክበር ቆይቷል። በዚህ የለውጥ ፕሮጀክት ላይ ስራው በኦክቶበር ወር ተጀመረ። ይህ እንደተጠናቀቀ፣ CWD የPFAS ደረጃዎችን ለመወሰን ናሙናዎችን መሰብሰብ ይጀምራል። ከ10 ppt በታች የሆኑ እና ምናልባትም "ምንም ግኝት ያለመኖር" ደረጃዎችን ለማየት እንጠብቃለን።

የ PFAS ደረጃዎች ከ10 ppt (ይህም ከተፈቀደው የአስተማማኝ ገደብ ግማሽ ነው) በታች እንደሆኑ እንደተረጋገጠ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ማጣሪያዎች፣ CWD የካምብሪጅ ውሃ ከMWRA ውሃ ጋር መቀላቀል ይጀምራል። ሁሉም 6 ማጣሪያዎች እስኪጠናቀቁ ድረስ ቀስ በቀስ የካምብሪጅ የውሃ ፍሰት እየጨመረ እና የ MWRA እየቀነሰ ይሄዳል፥፣ በዚህ ጊዜ CWD ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ መዋል እና በጣም አስተማማኝ እና ከፍተኛ ጥራት ያለው ውሃ ወደ ቧንቧዎ ማቅረብ አለበት።

**Cambridgema.gov/PFASFAQs** ላይ የበለጠ ይወቁ።



## አስፈላጊ የውሃ ጥበቃ ምክሮች

**የካምብሪጅ የውሃ ክፍል ነዋሪዎች እነዚህን የውሃ ጥበቃ ምክሮች ዓመቱን በሙሉ እንዲለማመዱ ያሳስባል፥-**

- ሳህኖች ሲሰሩ፣ ጥርስን ሲቦርሹ ወይም እቃ ሲያጠቡ ውሃ እንዲፈስ አይፍቀዱ።
- ይመልከቱ እና ማንኛውም ውሃ የሚያፈስ ከሆነ ለማየት ያዳምጡ ፣ መጸዳጃ ቤቶችን ብዙ ጊዜ ያረጋግጡ።
- አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ መጸዳጃ ቤቶችን ማጠብ.
- ብዙ የልብስ ማጠቢያዎችን ያካሂዱ።

ስለ ውሃ ጥበቃ በ **cambridgema.gov/water** ላይ የበለጠ ያንብቡ

**የከተማ አስተዳዳሪው መልዕክት** *ከሽፋን የቀጠለ*

በላቀ መደማመጥ፣ግልጽነት፣እንክብካቤ እና ክብር በኩል የህብረተሰቡን መስተጋብሮች በማሻሻል ላይ የሚያተኩር የፍትህ ስርዓት ስልጠና በ2010 በሀገሪቷ ከተገበሩ የመጀመሪያዎቹ መምሪያዎች አንዱ ነበር። እነዚህ ስልጠናዎች የማህበረሰቡን አመኔታና ግንኙነት በማሻሻል የወንጀል ድርጊቶች እና እስራት መቀነሳቸውን በሚያሳይ ሀገር-አቀፍ ዘርፈ ብዙ የጥናት ምርምር ላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከተሳተፉ ሶስት ከተሞች አንዱ ነበርን። ሌላኛው ምሳሌ የካምብሪጅ ሴፍቲ ኔት ትብብር ነው፣ ይህም የታዳጊዎችን እስራት በ90% የቀነሰ እና ወጣቶችን በጣልቃ ገብነት እና በመቀየሪያ ስልቶች የሚደግፍ ብሄራዊ አርአያ ነው። በአሰቃቂ የበፊት ታሪክ መረጃ ላይ የተመሰረተ እንክብካቤ እና የታዳጊዎች የፖሊስ ስልጠና መርሃ ግብራችን ላይ የሚፈስ መዋዕለ ንዋይን ጨምሮ ሌሎችም በርካቶች አሉ። ኮሚሽነር Elow እና የአመራር ቡድኗ ህጎቻችንን ለማስፈፀም ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰባችን አጠቃላይ ጤና እና ደህንነት ለመስራት ጥልቅ ቁርጠኝነት አላቸው። ገና ብዙ የሚቀሩን ስራዎች ቢኖሩም በትክክለኛው አቅጣጫ እና በትክክለኛ እሴቶች እየተጓዝን ነው።

ከተማዋ የተለያዩ ማህበረሰባችንን እና በአስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ለመናገር የሚሞክሩትን በርካታ ድምጾችን እንዴት በተሻለ መልኩ እንደምታሳትፍ እያሰላሰልኩም ነበር። እውነታው ግን ብዙ ሰዎች ያልተሰሙ እንደሆኑ ይሰማቸዋል፣እንዲሁም ማህበረሰቡ በማይስማማበት ጊዜ ውሳኔ የምናደርግበት መንገድ ላይም ሰፋ ያለ ተግዳሮት አለ። ወደ ፊት የጋራ ጉዳዮችን አብረን መፈለግ እንደምንቀጥል እንዲሁም አጣዳፊ ጉዳዮቻችንን እና ፍላጎታችንን ብቻ ሳይሆን አንዳችን ለሌላችን ያለንን የመረዳት ስሜት እና ለመልካም ሀሳቦቻችን እና በከተማችን ላለው ሁሉም ሰው ያለንን ክብር የሚያንፀባርቁ ጤናማ የሆኑ ማህበረሰባዊ ውይይቶች እንደሚኖሩን ተስፋ አደርጋለሁ። በከተማዋ በኩል ግንኙነታችንን፣ ግልጽነታችንን እና ምላሽ ሰጪነታችንን ለማሻሻል የሚሰራ ስራ እንዳለ ተገንዝቤያለሁ እና ይህም ለእኔ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

የዚህ አንድ አካል እንደመሆኔ መጠን፣ የበለጠ ተደራሽ በመሆኔ እና ከነዋሪዎች ጋር ለመ ቀመጥ እና አስተያየት ለማግኘት ጊዜ በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ። በመላው ከተማው ውስጥ መደበኛ ስብሰባ እና ሰላምታዎችን እያስተናገድኩ ነው። መርሃ-ግብሩን ለማየት እባክዎን **Cambridgema.gov/MeettheManager**ን ጎብኙ። እያንዳንዳችሁ የማ ህበረሰባችን አስፈላጊ ክፍሎች ናችሁ፣ እናም ከእናንተ ለመስማት እጓጓለሁ!



Yi-An Huang



ፎቶ፦ በካምብሪጅ አርትስ የተለገሰ።።

## ካምብሪጅ አዲሱን የፈጠራ ማዕከሉ የሆነ ውን The Foundryን ይከፍታል

በዚህ በልግ፣ በ Kendall አደባባይ የሚገኘው የከተማው አዲስ በራስ-የሚደገፍ የፈጠራ እና የትብብር ማዕከል የሆነውን The Foundry መክፈቻን ለማክበር 3,000 በላይ የካምብሪጅ ማህበረሰብ አባላት ተሰበሰቡ። 50,000 ስኩዌር ጫማ ቦታው በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና፣ ስነ-ጥበባት እና ሂሳብ እንዲሁም የእይታ እና የተግባር ስነ-ጥበባት፣ ስራ ፈጣሪነት፣ የስራ ግብረ ሃይል ትምህርት እና የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ዘርፎች እና ፕሮግራሞች ላይ እድሎችንይሰጣል። Foundry፣ ከካምብሪጅ ማሻሻያ ባለስልጣን ጋር በሽርክና የሚንቀሳቀስ፣ በከተማው ባለቤትነት የተያዘ ህንጻ እንደመሆኑ፣ የ Kendall አደባባይ ተለዋዋጭ የስራ እና የትምህርት አከባቢ ለነዋሪዎች በተለይም በሚገባ ላልተወከሉ ማህበረሰቦች ተደራሽ እንዲሆኑ ያመቻቻል። Foundry መርሀ-ግብሮች እና ቦታዎች ገቢን መሰረት ባደረጉ ቅናሾች በኩል ለማህበረሰብ አባላት ተደራሽ ሆነው እንዲቆዩ ያለመ ነው። በአርቲስት Elisa H. Hamilton የተፈጠረው እና በ Cambridge Percent-for-Art Program በኩል በካምብሪጅ የሥነ ጥበብ ምክር ቤት የተሰጠውን የተረት/ታሪክ መንገሪያ መርሃ ግብር የሆነውን Jukeboxን በ Foundry ውስጥ ማግኘት ይችላሉ። **Cambridgefoundry.org** ላይ የበለጠ ይወቁ።

## የካምብሪጅ የነዳጅ እርዳታ ፕሮግራም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች ለክረምት ማሞቂያ እንዲከፍሉ ይረዳል

የካምብሪጅ የነዳጅ እርዳታ ፕሮግራም ለ2022-2023 ወቅት ማመልከቻዎችን እየተቀበለ ነው። የቤት የኃይል እርዳታ ፕሮግራም በመባል የሚታወቀው መርሃ ግብር፣ የፌደራል የገቢ መመሪያዎችን የሚያሟሉ ነዋሪዎችን ከኖቬምበር 1 እስከ ኤፕሪል 30 ባለው ጊዜ ውስጥ የክረምት ማሞቂያ ሂሳባቸውን እንዲከፍሉ ይረዳቸዋል። ባለፉት አምስት አመታት የነዳጅ እርዳታ መርሃ ግብር ከ$4.8 ሚሊዮን በላይ የማሞቂያ ክፍያ እርዳታ ለካምብሪጅና ለሰመርቪል ነዋሪዎች አሰራጭቷል።

"ለዚህ ፕሮግራም ብቁ የሆኑ ሁሉም የካምብሪጅ እና ሰመርቪል ቤተሰቦች ገንዘብ ለመቆጠብና በክረምቱ ሙቀት እንዲያገኙ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማግኘታቸው ለእኛ አስፈላጊ ነው" በማለት የነዳጅ እርዳታ ፕሮግራም ስራ አስኪያጅ Claudia Cruz ትገልፃለች። "በሰራተኞቻችን አባላት ውስጥ ስፓኒሽ ተናጋሪዎች አሉን እናም በሚጠየቅበት ጊዜ ተጨማሪ የቋንቋ ድጋፍ መስጠት እንችላለን። በአካል የቀጠሮ ጥያቄዎችን ማስተናገድ እና ከቤት መውጣት የማይችሉ እና ማመልከቻቸውን ለማጠናቀቅ ድጋፍ የሚፈልጉ አመልካቾችን በቤት መጎብኘትም እንችላለን።

የነዳጅ እርዳታ መርሃ ግብሩ ደንበኞች እንደ ጋዝ እና ኤሌክትሪክ ክፍያ ቅናሾች፣ እንደ መከለያ እና ማሸጊያ ያሉ የአየር ሁኔታ ማሻሻያዎች፣ የግዛቱ የማሞቂያ ስርዓት ጥገና እና መቀየሪያ ፕሮግራም እና ሌሎችን የመሳሰሉ ጥቅማጥቅሞችን በሌሎች ኤጀንሲዎች በኩል እንዲያገኙ ይረዳል። ሙቀት በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ወይም አፋጣኝ የፍጆታ መዘጋት ያጋጠማቸው አመልካቾች በ24 ሰዓታት ውስጥ የነዳጅ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ፣ በ 617-665-6234 ይደውሉ ወይም **Cambridgema.gov/FuelAssistance**ን ይጎብኙ።

**ይህንን የCityView ጉዳይ በኦላይን በ *CityView* ይመልከቱ።**

## ከማህበረሰብ ማሰባሰቢያ መርሃ ግብሩ የሚገኘውን አስተዋጾ በመጠቀም በአካባቢው የፀሐይ ብርሃን ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ካምብሪጅ በማሳቹሴትስ የመጀመሪያ ከተማ ነች



ካምብሪጅ በማሳቹሴትስ ውስጥ ከኤሌክትሪክ ማሰባሰብ መረሃ ግብሩ የተገኘውን አስተዋጾ በመጠቀም በአካባቢው የፀሐይ ፕሮጀክት ላይ ኢንቨስት በማድረግ የመጀመሪያዋ ከተማ ነች። በሴፕቴምበር ወር ወደ Graham & Parks ትምህርት ቤት የተካተተው ባለ 540 ፓነል ተከላ በ41,000 የካምብሪጅ ማህበረሰብ የጅምላ ኤሌክትሪክ (CCE) መርሃ-ግብር ደንበኞች የተከፈለበት እና በባለቤትነት የተያዘ ነው። የ 243 ኪሎ ዋት የፀሐይ ኃይል ተከላው በየዓመቱ 280,000 ኪሎ ዋት በሰዓት ያመነጫል ተብሎ ይጠበቃል። የፀሐይ ኃይል ተከላው ከካርቦን-ነጻ የሆነ ኤሌክትሪክ በመላው የአገልግሎት እድሜው የአለም ሙቀት መጨመርን ከ4 ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ይቀንሳል፣ ይህም 426 መኪናዎችን ከመንገድ ላይ ከማንሳት ወይም ከ32,000 በላይ ዛፎችን ከመትከል ጋር እኩል ነው።

ከተማዋ በCCE መርሃ ግብር ላይ ተጨማሪ አዲስ ታዳሽ ሃይል ለመጨመር አዳዲስ መንገዶችን መፈለጓን ቀጥላለች። በ2017 የተጀመረው CCE ለካምብሪጅ ነዋሪዎች እና ንግዶች ኤሌክትሪክ አቅርቦት Eversource's Basic Serviceን በአማራጭነት የሚሰጥ በከተማ የሚተዳደር መርሃ-ግብር ነው። ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ ተሳታፊዎች ለዚህ የአካባቢ የፀሐይ ፕሮጀክት አስተዋፅኦ ሲያደርጉ ከ $30 ሚሊዮን በላይ የመብራት ሂሳባቸውን ቆጥበዋል። ነዋሪዎች እና ንግዶች በCCE ፕሮግራም እስከ 100% ታዳሽ ኤሌክትሪክን መርጠው መመዝገብ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ **Masspowerchoice.com/cambridge**ን ይጎብኙ።

# ክረምት እየመጣ ነው። ዝግጁ ነዎት?

የክረምቱ ወቅት እየተቃረበ በመሆኑ፣ ዝናብን ተከትሎ በረዶ እና በረዶን ማስወገድ በሚመለከት በከተማዋ ድንጋጌ መሰረት ስለሚኖሩባቸው ኃላፊነቶች ነዋሪዎችን እና የንብረት ባለቤቶችን እናስታውሳለን።



- ከንብረትዎ አጠገብ ያለውን የእግረኛ መንገድ እስከ ባዶ አስፋልት ከ3 - 4 ጫማ ስፋት ድረስ ያጽዱት። ይህም በቀን በረዶው መውረድ ካቆመ በ12 ሰአታት ውስጥ እንዲሁም በሌሊት ከወረደ ደግሞ ከ1 p.m. ሰአት በፊት መሆን አለበት።
- በሁሉም ጎኖች ያሉትን የማዕዘን ንብረቶችን እና በእግረኛ መንገዶች ላይ የሚገኙ የመወጣጫዎች መዳረሻዎችን ያፅዱ።
- ሁሉንም በረዶ በተፈጠረ በ6 ሰአታት ውስጥ ያስወግዱ ወይም ያቅልጡ። እርስዎ ርቀው ካሉ፣ አንድ ሰው ከንብረትዎ አጠገብ የእግረኛ መንገዶችን እና መወጣጫዎችን እንደሚያጸዳ ማረጋገጥ አሁንም የእርስዎ ኃላፊነት ነው። የከተማውን የእግረኛ መንገድ ማጽጃ ድንጋጌን ያለማክበር ቅጣቱ በቀን $50 ነው።
- የበረዶ እና የግግር በረዶ ማቅለጫ ምርቶችን በጥንቃቄ ይጠቀሙ። በረዶው በሚቀልጥበት ጊዜ፣ ከመንገድ፣ ከእግረኛ መንገድ እና ከመኪና መንገድ የሚመጡ እነዚህ ምርቶች በአቅራቢያው ወዳለው ተፋሰስ እና ወደ ውሃ መንገዳችን ይገባሉ። ለእንስሳት እና ለዕፅዋት መርዛማ ያልሆኑ ምርቶችን ለመግዛት ይሞክሩ።
- የጎርፍ መጥለቅለቅን ለመከላከል ተፋሰሶችን ነፃ በማድረግ ያግዙ።
- በረዶን በአካፋ ወደ ብስክሌት መንገድ አይገልብጡ።
- እባክዎን በአቅራቢያዎ ያሉ የእሳት ማጥፊያዎች ዙሪያ ያለውን በረዶ በማንሳት ያግዙ።




## በረዶ ስለመኖሩ ማንቂያ ማሳወቂያ እንዲደርስዎት ይመዝገቡ

የበረዶ ድንገተኛ የመኪና ማቆሚያ ክልከላ ማንቂያዎችን በስልክ፣ በጽሁፍ ወይም በኢሜይል በ **Cambridgema.gov/subscribe** ለመቀበል ይመዝገቡ ወይም ለአዳዲስ መረጃዎች በ Twitter ላይ **@CambMA** እና Facebook ላይ ይከተሉን። ህዝቡ ውይይቱን እንዲከታተል ለመርዳት ከተማዋ **#CambMASnow** የሚል ሃሽ መለያ በትዊተር ላይ እየተጠቀመች ነው።

## ለአዳዲስ መረጃዎች የካምብሪጅ የበረዶ ማዕከልን ይመልከቱ

የካምብሪጅ የበረዶ ማዕከል **Cambridgema.gov/snow** ስለ በረዶ የመኪና ማቆሚያ ገደቦች፣ አማራጭ ከመንገድ ዉጭ የመኪና ማቆምያ እና ስለተዘጉ ቦታዎች አዳዲስ መረጃዎችን ያካትታል።

## ከተማዋ ምን እንደምትሰራ፦

* ከተማዋ በረዶ በጀመረ በሶስት ሰአታት ውስጥ ሁሉንም ዋና ዋና መንገዶች በኬሚካል ታክማለች፣ በሁሉም የዝናብ ደረጃዎች በረዶ እንዲዛቅ ታደርጋለች፣ እንዲሁም ዝናቡ ካበቃ በኋላ የከተማዋን ንብረት የሚያዋስኑትን ሁሉንም መንገዶች እና የእግረኛ መንገዶችን ለማጽዳት ትሰራለች።
* የህዝብ አገልግሎት፣ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ይኖራል ተብሎ ከሚጠበቅ በረዶ በፊት brine (የጨው ውህድ) መንገዶች ላይ ይተገብራል ይህም በረዶ እና ግግር በረዶ ከመንገድ ንጣፎች ጋር እንዳይጣበቁ ይከላከላል። ከመንገድ ላይ ተወርውረው ከሚወጡ ወይም በበረዶ እና በግግር በረዶ ላይ ሊጣበቁ ከሚችሉት ጠጣር ጨዎች በተለየ፣ brine (የጨው ውህድ) ከዝናብ ጋር ሲገናኝ ወዲያውኑ መስራት ይጀምራል። ይህም ቀላል እና ይበልጥ ቀልጣፋ የበረዶ ማስወገድን ያስከትላል። በተጨማሪም፣ brine (የጨው ውህድ) መጠቀም በግምት 30% ያነሰ ጨው በመጠቀም የአካባቢ ተፅእኖን ይቀንሳል፣ እንዲሁም ወደ ዛፍ ጉድጓዶች እና የውሃ መስመሮች ውስጥ የሚፈሰውን ከፍተኛ ጨው ይቀንሳል።
* በረዶን በተቻለ መጠን በቅልጥፍና እና በብቃት የማስወገድ ሂደቶችን በቀጣይነት እንገመግማለን እንዲሁም የከተማው የእግረኛ መንገዶች እና ጎዳናዎች ለሁሉም ተጠቃሚዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና አመቺ ለማድረግ በአዳዲስ መሳሪያዎች እና ለአካባቢ ጥበቃ ተስማሚ በሆኑ ቴክኒኮችላይ ኢንቨስት እናደርጋለን።

## ለክረምት ከባድ ዝናቦች ይዘጋጁ

* ከባድ ዝናቡን ለማለፍ በቂ የማሞቂያ ነዳጅ እንዳለዎት ያረጋግጡ፤
* ባትሪዎች፣ የእጅ ባትሪዎች፣ የታሸጉ እቃዎች፣ የታሸገ ውሃ ያጠራቅሙ፤
* የጭስ እና የካርቦን ሞኖክሳይድ መመርመሪያዎች በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ፤
* አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶች አቅርቦት እንዳለዎት ያረጋግጡ።

## ሙቀት የለም?

በኪራይ ቤትዎ ውስጥ ምንም አይነት ሙቀት እንደሌለ ለማሳወቅ፣ ወደ ኢንስፔክሽን አገልግሎት መምሪያ በ617-349-6100 በመደወል የሰፈርዎ የቤቶች ተቆጣጣሪ እንዲገኝልዎት ይጠይቁ። ከሰዓታት በኋላ፣ እርስዎን በመወከል ተቆጣጣሪ እንዲያገኝልዎት ለካምብሪጅ የእሳት አደጋ መከላከያ መምሪያ በ 617-349-4900 ይደውሉ።

## ከበረዶ ነፃ የማድረግ ፕሮግራም እና በረዶ የማንሳት እርዳታ

ዝቅተኛ-ገቢ ያላቸው አረጋውያን ወይም አካል ጉዳተኞች ለከተማው ከበረዶ ነፃ የማድረግ ፕሮግራም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ፣ የካምብሪጅ ስለ እርጅና ምክር ቤትን በ 617-349-6220 ያግኙ።

የእርጅና ምክር ቤቱ፣ በረዶ የሚያስወግዱ ባለሙያ ኩባንያዎች እና በአካፋ በረዶ የሚያነሱ ተማሪዎችን ውስን ዝርዝር ለክፍያ ድርድር ማቅረብ ይችላል።




## እነዚህን ጠቃሚ የመንገድ ላይ የመኪና ማቆሚያ መመሪያዎችን አይርሱ፦

* በደንብ መታየት እንዲችሉ እና የበረዶ ማንሻዎች በረዶን ከእግረኛ መንገድ እንዲገፉ ለማስቻል ከመንገድ ጥግ ቢያንስ 20 ጫማ ርቀት ላይ ያቁሙ።
* ነጻ የመኪና ማቆሚያ ቦታን ለግል በተጠባባቂነት መያዝ ሕገ-ወጥ ነው፤ በመንገድ ላይ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ላይ የተተዉ ቁሶች ይወገዳሉ።

## ጉዳዮችን በኦንላይን ወይም የስማርት ስልክዎን በመጠቀም ሪፖርት ያድርጉ

* ጽዳት የሚያስፈልጋቸው የእግረኛ መንገዶች፣ የብስክሌት መንገዶች፣ ወይም መንገዶችን ተመልክተዋል? ችግርን ሪፖርት ማድረግ አንድ ደቂቃ ብቻ የሚወስድ ሲሆን መንገዶቻችን እና የእግረኛ መንገዶቻችን የበለጠ ደህንነታቸው የተጠበቀ ለማድረግ ይረዳል።
* ለiPhone ወይም አንድሮይድ ነፃ Commonwealth Connect app (የኮመንዌልዝ ግንኙነት መተግበሪያን) ያውርዱ ወይም በ Cambridgema.gov/311 ኦንላይን ሪፖርት ያድርጉ።

# የካምብሪጅ የእሳት አደጋ መምሪያ የቤት ውስጥ የእሳት አደጋ ትምህርትን ይዞ ተመልሷል

***የቤት ውስጥ ስልጠና ክፍት የስራ ቦታዎችን በፍጥነት ለመሙላት ይረዳል***

በኦክቶበር ወር የካምብሪጅ የእሳት አደጋ መምሪያ ጥብቅ የ11-ሳምንት የካምብሪጅ የእሳት አደጋ ትምህርት ጀምሯል ይህም የማሳቹሴትስ ግዛት የእሳት አደጋ አካዳሚ መርሆችን ያካተተ ይሁን እንጂ ብዙ ምልምሎች እንዲሳተፉ እና ክፍት የስራ መደቦች ከመደበኛው ጊዜ 12 ወራት ቀድመው እንዲሞሉ ለማድረግ የራሱ የሆኑ የተመሰከረላቸው የእሳት አደጋ አስተማሪዎችን በመጠቀም ነው።



ከ 1980 ጀምሮ የካምብሪጅ የእሳት አደጋ መከላከያ መምሪያ ለአዲስ ተቀጣሪዎች በMA Fire Academy ላይ ተመርኩዞ ቆይቷል።። ይህም ሂደት 10 ወራት የሚፈጅ ሲሆን ከአንድ ማህበረሰብ ስድስት አመልካቾችን ብቻ ይፈቅዳል።

የካምብሪጅ የእሳት አደጋ ትምህርት ምልመላ ክፍል 2022-01 የእለት ተእለት የአካል ብቃት ልምምዶች እና ከዚያም በማስከተል የክፍል ውስጥ እና የተግባር ስልጠናን ያቀፈ ነው። ሀያ የካምብሪጅ የእሳት አደጋ ምልምሎች ሁሉን አቀፍ የኋላ ታሪክ ምርመራ፣ የህክምና ምርመራዎች፣ የስነ-ልቦና ምርመራዎች እንዲሁም በኮመንዌልዝ የሰው ሃይል ክፍል የሚሰጠውን የአካል ብቃት ፈተናዎች አልፈዋል።

በጃንዋሪ 2023 ሲመረቁ፣ ምልምሎች የ Firefighter I/II ማረጋገጫ ያገኛሉ፤ የካምብሪጅ የእሳት አደጋ ተከላካይ እንደመሆናቸው ለስኬታቸው ወሳኝ ከሆኑ ሌሎች ስልጠናዎች መካከል እንደ የአደገኛ ቁሶች የክወና የደረጃ ስልጠና፣ ከውሃ ውስጥ ማዳን፣ የመጀመሪያ ምላሽ ሰጭ ስልጠና፣ የቀጥታ የእሳት አደጋ




**የካምብሪጅ የእሳት አደጋ መከላከያ መምሪያን እንዴት መቀላቀል እንደሚችሉ ይወቁ።**
**በ 617-349-4921 ይደውሉ።**

# ተመጣጣኝ ዋጋ ላላቸው ቤቶች ስኬት፡ የከተማው ምክር ቤት በማበረታቻ ቦታ ክፍፍል ላይ የሚደረጉ ለውጦችን በስራ ላይ ያውላል



የካምብሪጅ ከተማ ምክር ቤት በኦክቶበር 17፣ 2022 የማበረታቻ ቦታ ክፍፍል ድንጋጌን ማሻሻያ አጽድቋል፣ ይህም ለከተማው ተመጣጣኝ ዋጋ ላላቸው ቤቶች የገንዘብ ድጋፍ ይጨምራል። በከተማው የቦታ ክፍፍል ድንጋጌ የማበረታቻ የቦታ ክፍፍል ድንጋጌዎች ላይ በተደረጉት አዳዲስ ለውጦች መሰረት ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት መዋጮ መጠን በካሬ ጫማ ከ$21.02 ወደ $33.34 ጠቅላላ ወለል ስፋት ለአዳዲስ ትልቅ መኖሪያ ላልሆኑ ግንባታዎች ይጨምራል። በማበረታቻ የቦታ ክፍፍል ስር የተገኙ ገንዘቦች ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶችን ለመፍጠርና ለማቆየት በከተማው ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው የቤቶች የገንዘብ ድጋፍ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

በማርች 2020 ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው፣ የማበረታቻ የቦታ ክፍፍል ትልቅ የመኖሪያ-ያልሆኑ ግንባታዎች የሚፈጥሩትን የተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ፍላጎትን ለማካካስ የመኖሪያ ቤት መዋጮን ይፈልጋል። የማበረታቻ የቦታ ክፍፍል የቤቶች መዋጮ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የተመጣጣኝ ዋጋ መኖሪያ ቤቶችን ለማልማት ከ$20 ሚሊዮን በላይ ድጋፍ አድርጓል።

ይህ አዲስ ማሻሻያ 100% ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት መደራረብን ጨምሮ፣ ባለፉት ጥቂት አመታት ካምብሪጅ ባስቀመጣቸው በርካታ መገልገያዎች ላይ እና ለተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት በከተማው ውስጥ ያለው የገንዘብ ድጋፍ ይጨምራል። በ2023 በጀት ዓመት የካምብሪጅ ከተማ ከ$38 ሚሊዮን በላይ የከተማ ገንዘቦችን ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤቶችን ለመፍጠርና ለማስጠበቅ መድቧል። ባለተመጣጣኝ ዋጋ የመኖሪያ ቤቶች ባለአደራው ሲጠናቀቁ ከ500 በላይ መኖሪያ ቤቶችን ለማቆየት ወይም ለመፍጠር በአሁኑ ጊዜ በመካሄድ ላይ የሚገኙት የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች ላይ ከ$100 በላይ ለማዋል ቁርጠኝነት አለው።

**Cambridgema.gov/housing** ላይ የበለጠ ይወቁ።



## የጤና መምሪያ የኮቪድ-19 ማጠናከሪያ ክትባቶችን እና የኢንፍሉዌንዛ ክትባቶችን ይመክራል

የካምብሪጅ የህዝብ ጤና መምሪያ ሰዎች የኮቪድ-19 እና የኢንፍሉዌንዛ ክትባት እንዲከተቡ ያበረታታል።

**የኮቪድ-19 ክትባት** እድሜያቸው 6 ወር እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሁሉ ይመከራል። ዕድሜያቸው 5 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ማጠናከሪያ ክትባቶችን ማግኘት አለባቸው። ከበርካታ የኮቪድ-19 አይነቶች ጥበቃ የሚሰጥ አዲስ የ bivalent ማጠናከሪያ ክትባት በዚህ በልግ ተገኝቷል። የ bivalent ማጠናከሪያ ክትባት ለሁሉም አዋቂዎች እና 5 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ህጻናት ይመከራል። ሁሉንም የሚመከሩ የኮቪድ-19 ክትባቶችን መውሰድዎ ከፍተኛውን የጥበቃ ደረጃ ይሰጥዎታል።

**የኢንፍሉዌንዛ ክትባት** እድሜያቸው 6 ወር እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሁሉ ይመከራል። እድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ነዋሪዎች ከፍተኛ መጠን ያለው የኢንፍሉዌንዛ ክትባት መጠየቅ አለባቸው።

የኮቪድ-19 እና የኢንፍሉዌንዛ ክትባቶች በአከባቢ ውስጥ ፋርማሲዎች እና በብዙ የሀኪሞች ቢሮዎች በብዛት ይገኛሉ። የኮቪድ-19 ክትባት ቦታዎችን ለማግኘት፣ **Vaxfinder.mass.gov**ን ይጎብኙ። Cambridge Health Alliance (የካምብሪጅ የጤና ህብረት) እንዲሁ የኢንፍሉዌንዛ እና የኮቪድ-19 ክትባቶችን/ማጠናከሪያዎችን በካምብሪጅ ሆስፒታል፣ 1493 Cambridge Street እና East Cambridge Care Center, 163 Gore Street ውስጥ ባሉ ፋርማሲዎች ለህዝብ ያቀርባል።

## ወደ 988 ይደውሉ፡ ራስን የማጥፋት ቀውስ እና የስሜት ጭንቀት ላጋጠማቸው ግለሰቦች አንድ ግንኙነት፣ ሶስት አሃዞች

በጁላይ 2022 አዲስ ባለ ሶስት አሃዝ 988 ቁጥር በስሜታዊ ጭንቀት ወይም ራስን በራስ የማጥፋት ቀውስ ውስጥ ላለ ማንኛውም ግለሰብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተተግብሯል።

ህክምናዊ ያልሆኑ የሰለጠኑ አማካሪዎች ለሁሉም ደዋዮች ነፃ የሆነ ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ስሜታዊ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ ናቸው። ለሚወደው የሚጨነቅ ግለሰብ እና ያንን ሰው እንዴት መደገፍ እንዳለበት ወይም የት እንደሚረዳው የማያውቅ ግለሰብም እንዲሁ ሊጠቀምበት ይችላል።

ወደ 988 የሚደረጉ ጥሪዎች ወደ የብሄራዊ ራስን ማጥፋት መከላከል የህይወት መስመር (አሁን 988 ራስን ማጥፋት እና ቀውስ የህይወት መስመር በመባል የሚታወቀው) ይተላለፋሉ። የቀድሞው የህይወት መስመር ቁጥር 1-800-273- 8255 (1-800-273-TALK) በስሜታዊ ጭንቀት ወይም ራስን በራስ የማጥፋት ቀውስ ውስጥ ላሉ ሰዎች ሁልጊዜ የሚገኝ ሆኖ ይቆያል።

### *ወደ 988 ስደውል ምን ይሆናል?*

- ጥሪዎች በደዋዩ አካባቢ ኮድ መሰረት ወደ የጥሪ ማዕከል ይላካሉ።
- ሁሉም ጥሪዎች የሚመለሱት ሩህሩህ፣ ፍርድ አልባ ድጋፍ በሚሰጡ በጣም በሰለጠኑ ሰራተኞች አሊያም በጎ ፈቃደኞች ነው።
- ምንም እንኳ ቁጥሩ አጭር ቢሆንም፣ በማሳቹሴትስ ውስጥ ለብዙ አመታት ከነበረው ተመሳሳይ አገልግሎት ጋር የሚያገናኝ ነው።።

የ988 ራስን ማጥፋት እና ቀውስ የህይወት መስመር በኦንላይን ውይይት፣ **Suicidepreventionlifeline.org/chat** ማግኘት ይቻላል።

### *ከህይወት መስመር ጋር ስወያይ ምን ይሆናል?*

- በመጀመሪያ፣ ከችግር ጊዜ አማካሪው ጋር እስክናገናኞት የመስመር ላይ ይጠብቁ መልዕክት ያያሉ።
- ፍላጎቱ ከፍ ያለ ከሆነ፣ "Helpful Resources" (አጋዥ ምንጮች) የሚለውን ክፍል ማየት ወይም ለህይወት መስመር በ988 መደወል ይችላሉ።
- አማካሪው ውይይትዎን ይመልሳል፣ ያዳምጣል፣ ችግርዎ እንዴት ተፅዕኖ እያሳደረብዎ እንደሆነ ይገነዘባል፣ ድጋፍ ይሰጣል እና ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ምንጮችን ያጋራል።

ስለ 988 ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ **Mass.gov/988-suicide-and-crisis-lifeline.**ን ይጎብኙ።



## ከዲሴምበር 1፣ 2022 ጀምሮ የመኖሪያ ቤት የመኪና ማቆሚያ ፍቃዶችን ኦንላይን ያድሱ

የ2022 የመኖሪያ እና የጎብኝዎች የመኪና ማቆሚያ ፈቃዶች ማርች 31፣ 2023 ያበቃሉ። ከዲሴምበር 1፣ 2022 ጀምሮ ነዋሪዎች ፈቃዳቸውን ኦንላይን ማደስ ይችላሉ። የኦንላይን ማመልከቻዎች ለመስተናገድ ከሶስት እስከ አምስት ሳምንታት ይወስዳሉ። የ2023 ፈቃዶች ከጃንዋሪ 3፣ 2023 በፊት በፖስታ እንደማይላኩ እባክዎ ልብ ይበሉ።

ከጃንዋሪ 3፣ 2023 ጀምሮ፣ ፈቃዶች 344 Broadway, Cambridge ላይ City Hall Annex ውስጥ በሚገኘው  የከተማው የመኪናዎች ማቆሚያ እና ትራንስፓርት መምሪያ ውስጥ በአካል በመገኘት መታደስ ይችላሉ።።

ከጃንዋሪ 3 እስከ ማርች 31፣ 2023 "Parking by Permit Only" ("በፍቃድ ብቻ መኪና ማቆም") የሚል ምልክት ያደረጉ ቦታዎች ላይ የቆሙ መኪኖች የ2022 ወይም 2023 የፓርኪንግ ፈቃዶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ከኤፕሪል 1፣ 2023 ጀምሮ፣ "Parking by Permit Only" ("በፍቃድ ብቻ መኪና ማቆም") የሚል ምልክት ያደረጉ ቦታዎች ላይ የቆሙ መኪኖች የ2023 የነዋሪ ወይም የጎብኝዎች የመኪና ማቆሚያ ፈቃዶችን መጠቀም አለባቸው።

የ2023 የመኖሪያ ቤት የመኪና ማቆሚያ ፍቃድ የ Lauren Kershberg የሆነው ካምብሪጅ መስቀለኛ መንገድ የሚገኘውን ኩሬ ፎቶ ያሳያል። **Cambridgema.gov/rpp** ላይ የበለጠ ይወቁ።

# ጨርቃ ጨርቅ እና ፍራሾች ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንዳይጣሉ ተከልክለዋል

ከኖቬምበር 1፣ 2022 ጀምሮ በማሳቹሴትስ ሁሉም ጨርቃጨርቆች እና ፍራሾች ወደ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንዳይገቡ ተከልክለዋል።

የካምብሪጅ ከተማ የፍራሽ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ፕሮግራምን በ2019 እና የልብስ እና ጨርቃጨርቅ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ፕሮግራምን በ2021 ጀምሯል። ጨርቃጨርቆች ሁሉንም ልብሶች፣ ጫማዎች፣ ፎጣዎች፣ አንሶላዎች እና መለዋወጫዎች ያካትታሉ። እቃዎቹ ንፁህ እና ደረቅ መሆን አለባቸው፣ ይሁንና የተቀደደ ወይም የቆሸሸ ጨርቃ ጨርቅ እንኳን ዳግም ጥቅም ላይ ሊውል ወይም እንደ አዲስ እቃ ሊመረት ይችላል።




ሁለቱም መርሃ ግብሮች ከክፍያ ነጻ ናቸው፣ ይሁን እንጂ እቃዎች ካሉበት እንዲወሰዱ አስቀድመው በመርሐ ግብር መያዝ አለባቸው። በተጨማሪም፣ ነዋሪዎች ጨርቃ ጨርቆችን ለትርፍ በማይሠሩ ድርጅቶች ወይም በከተማው ስፖንሰር በተደረጉ 12 የማውረጃ ጣቢያዎች ውስጥ በአንዱ መስጠት ይችላሉ። ፍራሽ ወይም ጨርቃጨርቅ ለማስወሰድ ቀጠሮ ለመያዝ፣ **Cambridgema.gov/Recycle**ን ይጎብኙ።



# የአይጥ ዝርያዎችን ለመቆጣጠር የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮች

የአይጥ ዝርያዎችን መቆጣጠር ለማንኛውም ማህበረሰብ ከባድ ስራ ሊሆን ይችላል። ከታች ያሉት ጠቃሚ ምክሮች በዕለት ተዕለት ህይወታችን ላይ የአይጥ ዝርያዎችን (አይጠ-ሞገጥ፣አይጦች እና ሽኮኮዎች) ተጽእኖን ለመቀነስ መሞከር የሚችሉባቸው ናቸው።

- የምግብ እና የውሃ ምንጫቸውን ያስወግዱ። አይጥ ለመኖር በቀን አንድ አውንስ የምግብ ትራፊ ብቻ ይፈልጋል። ሁሉንም የምግብ ትራፊዎች ተቆላፊ የብስባሽ ጋሪዎች ውስጥ ማስቀመጥ አይጦችን ለመዋጋት በጣም የተሻሉ መንገዶች ውስጥ አንዱ ነው። በብስባሽ ጋሪዎች ላይ ያለው መቆለፊያ ሽታው እንዳይወጣ በማፈን አይጦች ምግብ ያለበትን ቦታ መለየት እና ማግኘት አዳጋች እንዲሆንባቸው ያደርጋል። በንብረትዎ ላይ ማንኛውንም ያቆረ ውሃ ያስወግዱ።
- ቆሻሻ መጣያዎ በትክክል መያዙን ያረጋግጡ። ሁሉም የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ክዳኖቻቸው መዘጋታቸውን ያረጋግጡ እንዲሁም በቆሻሻ መጣያ ውስጥ በተለይም በሚሰበሰቡበት ጠዋት ላይ ውጪ ላይ በሚቀመጡት ከመጠን ያለፉ የቆሻሻ መጣያ ከረጢቶች ውስጥ ምንም አይነት የምግብ እቃዎች አለመኖራቸውን ያረጋግጡ። የተነከሰ ቀዳዳ ያለው የቆሻሻ ከረጢት፣ ሪሳይክል ወይም ብስባሽ ጋሪ ካለዎት፣ ምትክ ለመጠየቅ የህዝብ ስራዎች መምሪያን ያነጋግሩ፦ **Cambridgema.gov/Recycle**።
- ለከተማው የግል ንብረት የአይጥ መቆጣጠሪያ ፕሮግራም ያመልክቱ። 4 ወይም ከዚያ በታች ያሉ ክፍሎች ባሉት ሕንፃዎች ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች ለከተማው የግል ንብረት የአይጥ መቆጣጠሪያ ፕሮግራም እንዲመዘገቡ ይበረታታሉ። ፕሮግራሙ በ60 ቀናት ጊዜ ውስጥ ነፃ ፍተሻና ቢያንስ 3 የመያዣ/የማጥመጃ/የመከታተያ ክትትሎችን ይሰጣል። በ **Cambridgema.gov/Rodents** የበለጠ ይወቁ።




# በብስክሌት ማለፊያ መንገድ የሚለያዩ ህንጻዎች ግንኙነት

የካምብሪጅ ከተማ መንገዶቻችንን ለሚራመዱ፣ ቢስክሌት ለሚነዱ፣ ለሚያሽከረክሩ ወይም የህዝብ መጓጓዣ ለሚጠቀሙ በሁሉም እድሜና አቅም ላሉ ሰዎች እንዲሆኑ አድርጎ ለመንደፍ ያለመ ነው። ግባችን? ጤናማ፣ ፍትሃዊ እንቅስቃሴን ለሁሉም እያሳደግን ከመጓጓዣ ጋር የተያያዙ ሞትን እና ከባድ ጉዳቶችን ለማስወገድ ነው።

የተነጠሉ የብስክሌት መንገዶችን መገንባት ግቡን የምናሳካበት አንዱ መንገድ ነው። ቢስክሌት የሚነዱ ሰዎችን ከተሽከርካሪ ትራፊክ ለመለየት ማገጃ ወይም ኩርባን መጠቀም ምቾትን ይጨምራል እና ብዙ ሰዎች ይህንን ንቁ እና ዘላቂ የመጓጓዣ ዘዴ እንዲጠቀሙ ያበረታታል። የሚፈልጉ ሰዎች ከመኪና ጉዞዎች በአስተማማኝ ሁኔታ መራቅ ከቻሉ፣ ካምብሪጅ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን መቀነስ፣ የአየር ጥራታችንን ማሻሻል እንዲሁም የተሽከርካሪ ትራፊክን መቀነስ ይችላል።

ይሁን እንጂ በከተማው ውስጥ በዘፈቀደ የተበተኑ የብስክሌት መንገዶችን መኖሩ ሰዎች ወደሚፈልጉበት ቦታ አያደርሱም፦ ለዚህም ነው ከተማዋ በካምብሪጅ ዙሪያ ካሉ አስፈላጊ መዳረሻዎች ጋር ሰዎችን የሚያገናኝ የተነጣጠሉ መስመሮችን መረብ እየገነባች ያለችው። የከተማው የብስክሌት ደህንነት ድንጋጌ ካምብሪጅ 25 ማይል የብስክሌት መንገዶችን በ2026 እንዲገነባ የሚጠይቅ ሲሆን ወደዛው ግብ ለመድረስ እድገት እያሳየን ነው። ከ2020 ጀምሮ፣ ከተማው በግምት 8 ማይል ርቀት የተነጠሉ የብስክሌት መንገዶችን ገንብቷል።

በበጋው ወቅት፣ ከተማዋ Porter አደባባይ አቅራቢያ Massachusetts Avenue ላይ በፈጣን-ግንባታ የተነጠሉ መንገዶችን ገነባች። በዚህ በልግ፣ ነዋሪዎችን እና ጎብኝዎችን ከቸርቻሮ ሱቆች፣ የስራ ቦታዎች፣ መናፈሻዎች እና አደባባዮች ጋር የሚያገናኝ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ቁልፍ የጉዞ መስመር ገንብተናል። ከተማዋ Inman Square፣ River Street እና MassAve4 በመባል በሚታወቀው የMass Ave ክፍሎችን የሚያካትት የረጅም ጊዜ የግንባታ ፕሮጀክቶች መካከል ላይ ትገኛለች።

እነዚህ ፕሮጀክቶች ጉልህ በሆነ የማህበረሰብ ግብአት የተቀየሱ ናቸው። የብስክሌት ደህንነት ድንጋጌ ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ ቢያንስ ሶስት የማህበረሰብ ስብሰባዎችን፣ ለአካባቢው ንግዶች እና ለሌሎች ድርጅቶች ማዳረስን፣ ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶችን እና አንዳንድ ጊዜ የማህበረሰብ የስራ ቡድኖችን ወደመፍጠር የሚያመሩ ብቅ-ባይ የመረጃ ክፍለ ጊዜዎችን ያካትታሉ።

### ቀጥሎ ምን ይመጣል?

በፈጣን ግንባታ የተለዩ የብስክሌት መስመሮች ወደ Brattle Street (በMason Street እና በSparks Street መካከል) የሚመጡ ሲሆን ከተማዋ በSparks Street እና በMt. Auburn Street መካከል ያለውን የፕሮጀክቱን ምዕራፍ 2 እቅድ እያጠናቀቀች ነው።

የካምብሪጅ ከተማ ለHampshire Street፣ Main Street እና Aberdeen Avenue መጪ ፈጣን የግንባታ ፕሮጀክቶች ንድፍ እና ተሳትፎ እየጀመረች ነው። የበለጠ ለማወቅ እና ለደብዳቤ መላኪያ ዝርዝሮች ለመመዝገብ **Cambridgema.gov/streetsandtransportation/projectsandprograms**ን ይጎብኙ።

# Lo más destacado de esta edición del boletín informativo CityView

**Lo que debe saber sobre las sustancias químicas PFAS**

- Las PFAS se encuentran en el agua, el aire y el suelo.
- Cambridge está trabajando para eliminar esta sustancia química nociva de nuestra agua.
- Para más información, visite **Cambridgema.gov/water**



**Conserve el agua durante todo el año**

- Nunca deje correr el agua mientras lava los platos, se lava las manos o se cepilla los dientes.
- Tire de la cadena del inodoro solo cuando sea necesario.

**El programa Fuel ayuda a los residentes con bajos ingresos a pagar las facturas de calefacción en invierno**

- El programa ayuda a los solicitantes a pagar las facturas de calefacción desde el 1 de noviembre hasta el 30 de abril.
- El personal habla varios idiomas y puede realizar visitas a domicilio para los solicitantes que no pueden salir de sus hogares.
- Para más información, visite **Cambridgema.gov/fuelassistance**



**Cambridge es la primera ciudad del estado que invierte en un nuevo tipo de proyecto solar**

- El proyecto solar reduce las emisiones responsables del calentamiento global.
- El programa Cambridge Community Electricity le ha ahorrado a los usuarios más de $30 millones.
- Para más información, visite **Masspowerchoice.com/Cambridge**



**Se acerca el invierno. ¿Está en condiciones de afrontar las nevadas?**

- Recuerde quitar la nieve de las aceras próximas a su propiedad.
- Para más información, visite **Cambridgema.gov/snow**



**¿Quiere convertirse en bombero en Cambridge?**

- El Cambridge Fire Department inauguró una nueva academia.
- Para más información, llame al 617-349-4921.

**El Cambridge City Council aprobó cambios en las tasas de incentivos de zonificación**

- Los fondos que se obtengan del aumento de las tasas se destinarán a financiar más viviendas asequibles.



**El Departamento de Salud recomienda refuerzos de la vacuna contra la COVID-19 y la gripe**

- Todo aquel que tenga 6 meses o más debe vacunarse contra la gripe y la COVID-19.
- Para más información, visite **vaxfinder.mass.gov**

**Puede llamar a la nueva línea 988 que atiende a personas con crisis suicidas o angustia emocional**

- También puede llamar al 988 para obtener ayuda para un ser querido.



**Renueve su permiso de estacionamiento residencial**

- Se puede renovar en línea: **Cambridgema.gov/rpp**




**No se recogerá ropa ni colchones en la recogida de residuos**

- Puede programar la recogida de prendas de vestir o colchones.
- Puede depositar la ropa en distintos puntos.
- Para más información, visite **Cambridgema.gov/recycling**



**Consejos para evitar la aparición de ratas**

- No deposite alimentos en los contenedores de residuos.
- Deposite alimentos únicamente en los contenedores de compostaje.
- Para más información, visite **Cambridgema.gov/rodents**



**Cambridge está construyendo nuevos carriles exclusivos para bicicletas**

- Separated bike lanes separate drivers from cyclists.
- Se instalaron nuevos carriles para bicicletas a lo largo de Massachusetts Avenue, cerca de Porter Square.

**Inscríbase para formar parte de una junta o comisión de la ciudad**

- Formar parte de una junta o comisión es una excelente manera de involucrarse más con su comunidad.
- Inscríbase hoy en **Cambridgema.gov/apply**

Vea los artículos completos en español en:
**Cambridgema.gov/CVSpanish**

# Destaques nesta edição da Newsletter CityView

### O que você deve saber sobre os Químicos PFAS

- O IPFAS é encontrado na água, ar e solo.
- Cambridge está trabalhando para remover este produto químico nocivo da nossa água.
- Saiba mais em **Cambridgema.gov/water**

### Por favor, Economize a Água o Ano Todo



- Nunca deixe a água correr enquanto lava a louça, lava as mãos ou escova os dentes.
- Dê descarga nos vasos sanitários somente quando necessário.

### O Programa Fuel ajuda moradores de baixa renda a pagar contas de aquecimento no inverno

- O programa ajuda os candidatos a pagar as contas de aquecimento de 1 de novembro a 30 de abril.
- Os funcionários falam vários idiomas e podem fazer visitas domiciliares para os candidatos que não moram em casa.
- Saiba mais em **Cambridgema.gov/fuelassistance**

### Cambridge é a primeira cidade do estado a investir em novo tipo de projeto solar



- O projeto solar reduz as emissões do aquecimento global.
- O Cambridge Community Electricity Program economizou aos usuários mais de US$ 30 milhões.
- Saiba mais em **Masspowerchoice.com/Cambridge**

### O inverno está chegando. Você está pronto para a neve?



- Lembre-se de remover a neve das calçadas próximas à sua propriedade.
- Saiba mais em **Cambridgema.gov/snow**

### Você está interessado em se tornar um bombeiro em Cambridge?



- O Cambridge Fire Department lançou uma nova academia.
- Para mais informações, ligue para 617-349-4921.

### O Cambridge City Council adota mudanças no zoneamento de incentivo Os Fundos de

- Taxas aumentadas apoiarão moradias mais acessíveis.

### Departamento de Saúde recomenda reforços e vacinas contra a gripe COVID-19



- Todos com 6 meses ou mais devem tomar vacinas contra a gripe e contra a COVID-19.
- Saiba mais em **vaxfinder.mass.gov**

### Ligue para o novo número 988 para pessoas em crise suicida ou sofrimento emocional

- Você também pode ligar para o 988 para obter ajuda para um ente querido.

### Renove sua permissão de estacionamento residencial



- Você pode renovar online, **Cambridgema.gov/rpp**

### Roupas e Colchões Banidos da Coleta de Lixo




- Você pode agendar uma coleta de roupas ou colchões.
- Você pode deixar roupas em vários locais.
- Saiba mais em **Cambridgema.gov/recycling**

### Dicas para Controle de Ratos



- Não coloque comida no lixo.
- Coloque os alimentos apenas em caixas de compostagem.
- Saiba mais em **Cambridgema.gov/rodents**

### Cambridge está construindo novas ciclovias separadas Ciclovias



- Separadas separam motoristas de ciclistas.
- Novas ciclovias foram instaladas ao longo da Massachusetts Avenue, perto de Porter Square.

### Inscreva-se para servir em um Conselho ou Comissão da Cidade

- Servir em um conselho ou comissão é uma ótima maneira de se envolver mais com sua comunidade.
- Inscreva-se hoje em **Cambridgema.gov/apply**

Veja os artigos completos em português em:
**Cambridgema.gov/CVPortuguese**

# Pwen Esansyèl nan nimewo Bilten Enfòmasyon CityView sa a

**Sa ou ta dwe konnen sou pwodui chimik PFAS yo**

- Yo jwenn PFAS la nan dlo, lè, ak nan tè.
- Cambridge ap travay pou retire pwodui chimik danjere sa a nan dlo nou an.
- Aprann plis sou **Cambridgema.gov/water**

**Tanpri Konsève Dlo pandan tout ane a**



- Pa janm kite dlo koule pandan w ap lave veso, w ap lave men w oswa pandan w ap bwose dan.
- Flòch twalèt yo sèlman lè sa nesesè.

**Pwogram Fuel la ede rezidan ki gen revni fèb yo peye bòdwo chofaj ivè yo a**

- Pwogram nan ede aplikan yo peye bòdwo chofaj yo soti 1ye novanm jiska 30 avril.
- Anplwaye yo pale plizyè lang epi yo ka fè vizit lakay pou aplikan ki rete lakay yo.
- Aprann plis sou **Cambridgema.gov/fuelassistance**

**Cambridge se premye vil nan eta a ki envesti nan nouvo tip pwojè solèy**



- Pwojè solèy la diminye emisyon rechofman planèt la.
- Pwogram Cambridge Community Electricity a fè itilize yo economize plis pase $30 milyon.
- Aprann plis sou **Masspowerchoice.com/Cambridge**

**Sezon Ivè Prèske Rive. Èske Ou Pare pou Lanèj?**



- Sonje pou retire nèj ki sou twotwa bò kote kay ou ye.
- Aprann plis nan **Cambridgema.gov/snow**

**Ou enterese vin yon Ponpye nan Cambridge?**



- Cambridge Fire Department lanse yon nouvo akademi.
- Pou plis enfomasyon rele nan 617-349-4921.

**Cambridge City Council Adopte Chanjman nan Pousantaj Ensitasyon Zòn yo**

- Lajan ki soti nan ogmantasyon pousantaj yo pral sipòte lojman ki pi bon mache.

**Depatman Sante a Rekòmande Ranfòsman vaksen kont COVID-19 ak Grip yo**



- Tout moun ki gen 6 mwa oswa plis ta dwe pran vaksen Grip ak COVID-19 la.
- Aprann plis sou **vaxfinder.mass.gov**

**Rele Nouvo Nimewo 988 pou Moun ki Sibi Kriz Swisid oswa Detrès Emosyonèl**

- Ou ka rele 988 tou pou jwenn èd pou yon moun ou renmen.



**Renouvle Pèmi pou Pakin Rezidansyèl Ou An**

- Ou ka renouvle anliy sou, **Cambridgema.gov/rpp**

**Rad ak Matla yo Entèdi nan Koleksyon Fatra**




- Ou ka planifye yon ranmasaj rad oswa matla.
- Ou ka depoze rad nan divès kote.
- Aprann plis sou **Cambridgema.gov/recycling**

**Konsèy pou Kontwole Rat**



- Pa mete manje nan fatra ou.
- Mete manje nan poubèl fatra sèlman
- Aprann plis sou **Cambridgema.gov/rodents**

**Cambridge ap Konstwi Yon Lòt Liy pou Bisiklèt**



- Liy pou bisiklèt yo separe chofè yo ak siklis yo.
- Nouvo liy bisiklèt yo te enstale nan Massachusetts Avenue tou pre Porter Square.

**Aplike pou Sèvi nan Konsèy oswa Komisyon yon Vil**

- Sèvi nan yon konsèy oswa yon komisyon se yon bon fason pou patisipe plis nan kominote w la.
- Aplike jodiya sou **Cambridgema.gov/apply**

Gade tout atik ann Angle sou:
**Cambridgema.gov/CVHaitianCreole**

# በ CityView ጋዜጣ ላይ ዋና ዋና ዜናዎች

## ስለ PFAS ኬሚካል ማወቅ ያለብዎት ነገር

- PFAS በውሃ፣ አየር እና አፈር ውስጥ ይገኛል።
- Cambridge ይህንን ጎጂ ኬሚካል ከውሃችን ውስጥ ለማስወገድ እየሰራ ነው።
- የበለጠ ለማወቅ **Cambridgema.gov/water** ን ይጎብኙ

## እባክዎን ውሃን ዓመቱን ሙሉ በአግባቡ ይጠቀሙ



- እቃ ሲያጥቡ፣ እጅ ሲታጠቡ ወይም ጥርስዎን ሲቦርሹ ውሃን ሳያባክኑ ይጠቀሙ።
- አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ መጸዳጃ ቤቶች ላይ ውሃ ይጠቀሙ።

## የ Fuel ፕሮግራም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች ለክረምት ማሞቂያ ሂሳቦች እንዲከፍሉ ይረዳል

- ፕሮግራሙ አመልካቾች ከኖቬምበር 1 እስከ ኤፕሪል 30 ድረስ የማሞቂያ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ይረዳል።
- ሰራተኞቹ ብዙ ቋንቋዎችን ይናገራሉ እና ለቤት ውስጥ አመልካቾች የቤት ጉብኝት ማድረግ ይችላሉ።
- የበለጠ ለማወቅ **Cambridgema.gov/fuelassistance** ን ይጎብኙ

## Cambridge በአዲስ ዓይነት የፀሐይ ፕሮጀክት ላይ ኢንቨስት በማድረግ በግዛት የመጀመሪያዋ ከተማ ነች



- የፀሐይ ፕሮጀክቱ የአለም ሙቀት መጨመርን ይቀንሳል።
- የ Cambridge Community Electricity ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን ከ $30 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ ታድጓል።
- የበለጠ ለማወቅ **Masspowerchoice.com/Cambridge** ን ይጎብኙ

## ክረምቱ እየመጣ ነው። ለበረዶው ተዘጋጅተዋል?



- ከንብረትዎ አጠገብ የሚገኘውን የእግረኛ መንገዶችን ላይ የሚገኘውን በረዶ በአካፋ መዛቅ እንዳለብዎት ያስታውሱ።
- የበለጠ ለማወቅ **Cambridgema.gov/snow** ን ይጎብኙ

## በ Cambridge ውስጥ የእሳት አደጋ ተከላካዮች ለመሆን ፍላጎት አለዎት?



- የ Cambridge Fire Department አዲስ አካዳሚ አስጀምሯል።
- ለበለጠ መረጃ: በ 617-349-4921 ይደውሉ።

## የ Cambridge City Council በማበረታቻ የ የዞን ዋጋዎች

- ላይ ለውጦችን ተግባራዊ አድርጓል ከተጨመሩ ተመኖች የሚገኘው ገንዘብ የበለጠ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤትን ይደግፋል።

## የጤና ዲፓርትመንት የ COVID-19 መከላከያ እና የፍሉ ክትባቶችን ይመክራል



- 6 ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሁሉም ሰው የፍሉ እና የ COVID-19 ክትባቶችን መውሰድ አለበት።
- የበለጠ ለማወቅ **vaxfinder.mass.gov** ን ይጎብኙ

## ራስን የማጥፋት ቀውስ ወይም የስሜት ጭንቀት ላጋጠማቸው ሰዎች አዲስ 988 ቁጥር ላይ ይደውሉ

- ለምትወዱት ሰው እርዳታ ለማግኘትም 988 ላይ መደወልም ይችላሉ።

## የመኖሪያ ፓርኪንግ ፈቃድዎን ያድሱ



- በ **Cambridgema.gov/rpp** መስመር ላይ ማደስ ይችላሉ

## አልባሳት እና ፍራሽ ከቆሻሻ ኮሌክሽን




- ታግደዋል ልብስ ወይም ፍራሽ ለመውሰድ ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ።
- ልብሶችን በተለያዩ ቦታዎች መጣል ይችላሉ።
- የበለጠ ለማወቅ **Cambridgema.gov/recycling** ን ይጎብኙ

## አይጦችን ለመቆጣጠር የሚረዱ ምክሮች



- ምግብን ወደ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ አያስቀምጡ።
- ምግብን በማዳበሪያ bins ውስጥ ብቻ ያስቀምጡ።
- የበለጠ ለማወቅ **Cambridgema.gov/rodents** ን ይጎብኙ

## Cambridge አዲስ የተለያየ የብስክሌት መስመሮችን እየገነባ ነው



- የተለያዩ የብስክሌት መስመሮች አሽከርካሪዎችን ከብስክሌት ነጂዎች ይለያሉ።
- አዲስ የብስክሌት መስመሮች በ Massachusetts Avenue በ Porter Square አጠገብ ተገንብተዋል።

## በከተማ ቦርድ ወይም ኮሚሽን ላይ ለማገልገል ያመልክቱ

- በቦርድ ወይም በኮሚሽን ማገልገል ከማህበረሰብዎ ጋር የበለጠ ለመሳተፍ ጥሩ መንገድ ነው።
- ዛሬ **Cambridgema.gov/apply** ላይ ያመልክቱ

ሙሉ ጽሁፎችን በአማርኛ በ:
**Cambridgema.gov/CVAmharic** ይመልከቱ

# النقاط البارزة في هذا العدد من CityView Newsletter

## ما يجب معرفته عن المادة الكيميائية PFAS

- PFAS موجودة في الماء والهواء والتربة.
- تعمل Cambridge على إزالة هذه المادة الكيميائية الضارة من مياهنا.
- اعرف المزيد على **Cambridgema.gov/water**



## يرجى الحفاظ على المياه على مدار العام

- لا تدع الماء ينساب أبدًا أثناء غسل الأطباق أو غسل اليدين أو تنظيف الأسنان.
- اغسل المراحيض عند الحاجة فقط.



## يساعد برنامج Fuel السكان ذوي الدخل المنخفض على دفع فواتير التدفئة الشتوية

- يساعد البرنامج المتقدمين على دفع فواتير التدفئة من 1 نوفمبر حتى 30 أبريل.
- يتحدث الموظفون عدة لغات ويمكنهم القيام بزيارات منزلية للمتقدمين المقيمين في المنزل.
- اعرف المزيد على **Cambridgema.gov/fuelassistance**



## Cambridge هي أول مدينة في الولاية تستثمر في نوع جديد من مشروع الطاقة الشمسية

- يقلل مشروع الطاقة الشمسية من انبعاثات غازات الدفيئة.
- وفر برنامج مجتمع الكهرباء في Cambridge مبلغا يزيد عن 30 مليون دولار.
- اعرف المزيد على **Masspowerchoice.com/Cambridge**



## الشتاء قادم. هل أنت مستعد للثلج؟

- تذكر أن تجرف الثلج من الأرصفة المجاورة لممتلكاتك.
- اعرف المزيد على **Cambridgema.gov/snow**



## هل أنت مهتم بأن تصبح رجل إطفاء في Cambridge؟

- اطلق Cambridge Fire Department أكاديمية جديدة.
- للمزيد من المعلومات اتصل على الرقم 617-349-4921.

## يتبنى Cambridge City Council تغييرات في معدلات

- تقسيم المناطق الحافزة ستدعم الأموال من المعدلات المتزايدة إسكانًا أكثر بأسعار معقولة.



## توصي وزارة الصحة بمعززات المناعة ضد COVID-19 ولقاحات الإنفلونزا.

- يجب أن يحصل كل شخص يبلغ من العمر 6 أشهر أو أكثر على لقاحات الإنفلونزا و COVID-19.
- اعرف المزيد على **vaxfinder.mass.gov.**

## اتصل برقم 988 الجديد للأشخاص الذين يعانون من أزمة انتحارية أو ضائقة عاطفية

- يمكنك أيضًا الاتصال بالرقم 988 للحصول على مساعدة لمن تحب.



## جدد تصريح وقوف السيارات الخاص بك

- يمكنك تجديده عبر الإنترنت، **Cambridgema.gov/rpp**




## الملابس والمراتب المحظورة من مجموعة القمامة

- يمكنك تحديد موعد لاستلام الملابس أو الملاءات.
- يمكنك ترك الملابس في مواقع مختلفة.
- اعرف المزيد على **Cambridgema.gov/recycling**



## نصائح للتحكم في الفئران

- لا تضع الطعام في سلة المهملات.
- ضع الطعام في صناديق السماد فقط.
- اعرف المزيد على **Cambridgema.gov/rodents**



## تبني Cambridge ممرات دراجات منفصلة جديدة

- تفصل ممرات دراجات منفصلة السائقين عن راكبي الدراجات.
- تم إنشاء ممرات New bike lanes were installed along جديدة للدراجات على طول Massachusetts Avenue و Porter Square.

## التقديم للخدمة في مجلس المدينة أو اللجنة

- الخدمة في لجنة مجلس الإدارة هي طريقة رائعة للمشاركة بشكل أكبر في مجتمعك.
- قدم طلبك اليوم على **Cambridgema.gov/apply**

اقرأ المقالة الكالة باللغة الإنجليزية على الرابط: **Cambridgema.gov/CVArabic**

# CityView নিউজলেটারের এই সমস্যার হাইলাইটসমূহ

### PFAS রাসায়নিক সম্পর্কে আপনার যা জানা উচিত

- PFAS পানি, বায়ু এবং মাটিতে পাওয়া যায়।।
- Cambridge আমাদের পানি থেকে এই ক্ষতিকর রাসায়নিক অপসারণের জন্য কাজ করছে।
- **Cambridgema.gov/water** -এ আরও জানুন

### অনুগ্রহ করে সারা বছর পানি সংরক্ষণ করুন



- থালা-বাসন পরিষ্কার, হাত ধোয়া বা দাঁত ব্রাশ করার সময় কখনই পানি ছেড়ে রাখবেন না।
- শুধুমাত্র প্রয়োজন হলেই টয়লেট ফ্লাশ করুন।

### Fuel প্রোগ্রাম স্বল্প-আয়ের বাসিন্দাদের শীতকালীন হিটিং বিল পরিশোধে সহায়তা করে

- প্রোগ্রামটি আবেদনকারীদের 1 নভেম্বর থেকে 30 এপ্রিল পর্যন্ত হিটিং বিল পরিশোধ করতে সহায়তা করে।
- কর্মীরা একাধিক ভাষায় কথা বলে এবং অসুস্থতাজনিত কারণে গৃহে অবস্থানরত আবেদনকারীদের ক্ষেত্রে হোম ভিজিট করতে পারে।
- **Cambridgema.gov/fuelassistance** -এ আরও জানুন

### স্টেটের প্রথম সিটি হিসেবে Cambridge নতুন ধরনের সৌর প্রকল্পে বিনিয়োগ করেছে



- সৌর প্রকল্প বৈশ্বিক উষ্ণায়নের জন্য জন্য দায়ী নির্গমন হ্রাস করে।
- Cambridge Community Electricity প্রোগ্রাম ব্যবহারকারীদের $30 মিলিয়নেরও বেশি সাশ্রয় করেছে।
- **Masspowerchoice.com/Cambridge** -এ আরও জানুন

### শীত আসছে। আপনি কি তুষারের জন্য প্রস্তুত?



- আপনার বাড়ির পাশের ফুটপাথ থেকে তুষার সরানোর কথা মনে রাখবেন।
- **Cambridgema.gov/snow** -এ আরও জানুন

### Cambridge-এ দমকলকর্মী হতে চান?



- Cambridge Fire Department একটি নতুন একাডেমি চালু করেছে।
- আরও তথ্যের জন্য, কল করুন 617-349-4921 নম্বরে।

### Cambridge City Council ইনসেনটিভ জোনিং রেটে পরিবর্তন সমন্বয় করে

- বর্ধিত রেটের ফান্ড আরও সাশ্রয়ী আবাসনকে সমর্থন করবে।

### স্বাস্থ্য বিভাগ COVID-19 বুস্টার এবং ফ্লু শট সুপারিশ করে



- 6 মাস বা তার বেশি বয়সের প্রত্যেকেরই ফ্লু এবং COVID-19 টিকা নেওয়া উচিত।
- **vaxfinder.mass.gov**-এ আরও জানুন

### যারা আত্মঘাতী অবস্থা বা মানসিক যন্ত্রণা ভোগ করছেন তারা নতুন 988 নম্বরে কল করুন

- আপনি প্রিয়জনের জন্য সাহায্য পেতেও 988 নম্বর কল করতে পারেন।

### আপনার আবাসিক পার্কিং পারমিট নবায়ন করুন



- আপনি অনলাইনে নবায়ন করতে পারেন, **Cambridgema.gov/rpp**

### আবর্জনার ঝুড়ি থেকে জামাকাপড় এবং ম্যাট্রেস সংগ্রহ নিষিদ্ধ করা হয়েছে




- আপনি জামাকাপড় এবং ম্যাট্রেস পিকআপের জন্য একটি সময় নির্ধারণ করতে পারেন।
- আপনি বিভিন্ন স্থানে পোশাক রেখে দিতে পারেন।
- **Cambridgema.gov/recycling** -এ আরও জানুন

### ইঁদুর নিয়ন্ত্রণের টিপস



- আপনার আবর্জনার ঝুড়িতে খাবার ফেলবেন না।
- শুধুমাত্র কম্পোস্ট বিনে খাবার রাখুন।
- **Cambridgema.gov/rodents** -এ আরও জানুন

### Cambridge নতুন আলাদা বাইক লেন তৈরি করছে



- আলাদা বাইক লেন ড্রাইভারদেরকে সাইক্লিস্টদের থেকে আলাদা করে।
- Porter Square-এর কাছে Massachusetts Avenue বরাবর নতুন বাইক লেন স্থাপন করা হয়েছে।

### সিটি বোর্ড বা কমিশনে কাজের জন্য আবেদন করুন

- বোর্ড বা কমিশনে কাজ করা আপনার কমিউনিটির সাথে আরও সংশ্লিষ্ট হওয়ার একটি দুর্দান্ত উপায়।
- **Cambridgema.gov/apply** -এ আবেদন করুন

বাংলায় সম্পূর্ণ নিবন্ধটি এখানে দেখুন: **Cambridgema.gov/CVBangla**

# 本期 CityView 通讯的亮点

### 您应该了解的关于 PFAS 化学品的知识

- PFAS 存在于水、空气和土壤中。
- Cambridge 正在努力从我们的水中去除这种有害化学品。
- 访问 **Cambridgema.gov/water** 了解更多信息

### 请全年节约用水



- 洗碗、洗手或刷牙时切勿长开水龙头。
- 仅在需要时冲马桶。

### Fuel计划帮助低收入居民支付冬季取暖费

- 该计划帮助申请人支付从 11 月 1 日到 4 月 30 日的取暖费。
- 工作人员会说多种语言，可以为居家申请者进行家访。
- 访问 **Cambridgema.gov/fuelassistance** 了解更多信息

### Cambridge是该州第一个投资新型太阳能项目的城市



- 太阳能项目减少了全球暖化排放。
- Cambridge Community Electricity计划为用户节省了超过$30M。
- 访问 **Masspowerchoice.com/Cambridge** 了解更多信息

### 冬天即将来临。你准备好迎接下雪天了吗？



- 记得铲除您住家附近人行道上的积雪。
- 访问 **Cambridgema.gov/snow** 了解更多信息

### 您有兴趣成为Cambridge的消防员吗？



- Cambridge Fire Department成立了一所新学院。
- 有关更多信息，请致电 617-349-4921。

### CambridgeCityCouncil通过改变激励分区利率

- 提高利率的资金将支持更多的经济适用房。

### 卫生部建议接种COVID-19加强针和流感疫苗



- 年满6个月或以上的人都应该接种流感和 COVID-19疫苗。
- 访问 **vaxfinder.mass.gov** 了解更多信息

### 为有自杀危机或情绪困扰的人致电新的988号码

- 您也可以致电988为亲人寻求帮助。



### 更新您的住宅停车许可证

- 您可以在线更新， **Cambridgema.gov/rpp**

### 禁在垃圾场丢弃衣物和床垫




- 您可以安排收取衣物或床垫。
- 您可以把衣服放在不同的地方。
- 访问 **Cambridgema.gov/recycling** 了解更多信息

### 防治老鼠的技巧



- 不要将食物放入垃圾桶。
- 仅将食物放入堆肥箱。
- 访问 **Cambridgema.gov/rodents** 了解更多信息

### Cambridge正在建造新的独立自行车道



- 独立的自行车道将驾驶人与骑自行车的人分开。
- 沿着Porter Square附近的Massachusetts Avenue安装了新的自行车道。

### 申请在市议会或委员会任职

- 在董事会或委员会任职是让您更积极参与社区的好方法。
- 立即在 **Cambridgema.gov/apply** 申请

通过以下网址查看完整的英文文章：
**Cambridgema.gov/CVChinese**

# City View

A publication of the Office of the City Manager, City of Cambridge


795 Massachusetts Avenue • Cambridge, MA 02139
617-349-4300 • Cambridgema.gov
Cambridgema.gov @CambMA



አመልካች እዚህ ላይ ይቀመጣል

አድራሻ እዚህ ላይ ይቀመጣል



የከተማ አስተዳዳሪ Yi-An Huang

የካምብሪጅ ከተማ ምክር ቤት፦

ከንቲባ Sumbul Siddiqui
ምክትል ከንቲባ Alanna M. Mallon

የምክር ቤት አባል Burhan Azeem
የምክር ቤት አባል Dennis J. Carlone
የምክር ቤት አባል Marc C. McGovern
የምክር ቤት አባል Patricia M. Nolan

የምክር ቤት አባል E. Denise Simmons
የምክር ቤት አባል Paul F. Toner
የምክር ቤት አባል Quinton Y. Zondervan


## በከተማ ቦርድ ወይም ኮሚሽን ውስጥ ማገልገልን ያስቡበት

በቦርድ ወይም በኮሚሽን ውስጥ ማገልገል አርኪ ተሞክሮ እና ለህብረተሰባችን አስተዋፆ ለማድረግ ጥሩ መንገድ ሊሆን ይችላል። የቦርድ አባላት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች በከተማው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ እድሉ አላቸው። ከተማዋ ከ500 በላይ አባላት ያሏቸው 80 ቦርዶች እና ኮሚሽኖች አሏት።

የካምብሪጅ ከተማ የፀረ ዘረኝነት፣ የብዝሃነት፣ የፍትሃዊነት እና የመደመር ባህልን ለማሳደግ ቁርጠኛ ናት። የቦርዱ እና የኮሚሽኑ አባላት የተለያየ ማንነት፣ ባህል፣ ታሪክና አስተሳሰብ ካላቸው ግለሰቦች ጋር የመተባበር አቅም ሊኖራቸው ይገባል።

የካምብሪጅ ሲቪክ ገጽታን በመቅረጽ ረገድ ወሳኝ ሚና ለመጫወት ዝግጁ ነዎት? ከሆነ፣ አሁን ያለን ክፍት የስራ ቦታ ይመልከቱ። ቦርዶች እና ኮሚሽኖች በአጠቃላይ የትምህርት እና የቴክኒካዊ የኋላ ታሪክ ባያስፈልጋቸውም አብዛኛዎቹ የካምብሪጅ ነዋሪነትን ይጠይቃሉ።

**ዛሬውኑ በ Cambridgema.gov/Apply ያመልክቱ።**

# Multilingual Highlights Inside on Page 9-15



**Página 9**
Lea la información en español

**Página 10**
Leia as informações em português

**Paj 11**
Li enfòmasyon an kreyòl ayisyen

**ገፅ 12**
መረጃውን በአማርኛ ያንብቡ

**13 صفحة**
قراءة المعلومات باللغة العربية

**পৃষ্ঠা 14।**
বাংলায় তথ্য পড়ুন

**第 15 页**
阅读 中文信息



**መረጃ ይኑርዎት፡፡ አዳዲስ መረጃ በኢሜይል እንዲደርስዎት በ Cambridgema.gov/subscribe ይመዝገቡ**